የሚጠይቁ መሆናቸውም እርግጥ ነው:: የግንኙነትና የሃሣብ ለውውጥ መጥፋት፣ የዘመቻውና የመምሪያው ሰማይና ምድር መራራቅ፣ አንዳንድ የመምሪያ አባላትም ኃላፊነትን ሳለመቀበል የሚያደርጉት ቅጥፈት ብዛታቸን የዘመቻ ጣቢያ ኃላፊዎች አስመርሮአቸዋል::

የመምሪያውና የዘመቻው ችግር ከሌሎች ሁኔታዎች ተነጥሎ በአየር የተንጠለጠለ አይደለም:: የምርጥ መኮንኖችን መንግሥት በሮክራሲያዊነት የሚያሳይ አንዱና አንዱ ብቻ ማስረጃ እንጂ! በዚህ አንፃር ዘማቾችና ተማሪዎች ተከከለኛ ጥያቄያቸውን ለማስፈፀም ማለትም፣

— የገበሬዎች መደራጀትና መታጠቅ፣

— የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ፣

— የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መቋቋም ገሃዱ እንዲሆን ትግላቸውን ማጠናከር ታሪካዊ ግዳጃቸው ነው:: ኢሕአፓ ከዘማቾች ጎን ነው!

ሰፊው ሕዝብ ያቸንፋል!